# ልጅዎ መዋለ ህፃናት የመግባት መብት አለው

1. **ልጄ መዋለ ህፃናት መግባት ያለበት ለምንድን ነው?**

- መዋለ ህፃናት ልጆች የሚጫወቱበት፣ ጓደኛ የሚያፈሩበት እንዲሁም የማህበራዊ ግንኙነታቸውን እና የመማር ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ስፍራ ነው፡፡
- ልጅዎ የኖርዌን ቋንቋ ይማራል እንዲሁም ከኖርዌይ ባህል ጋር ይለማመዳል፡፡ መዋለ ህፃናት መግባት ልጅዎን ትምህርት ለመጀመር ዝግጁ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

2. **በመዋለ ህፃናት ውስጥ የልጄ ደህንነት ይጠበቃል?**

አዎን፤ ሁሉም ልጆች ደህንነታቸው ተጠብቆ ተገቢ የሆነ እንክብካቤ መልካም  እና ብቁ  በሆኑ አዋቂዎች ይደረግላቸዋል፡፡

3. **ልጄ በመዋለ ህፃናት ውስጥ ውጤታማ መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**

በመዋለ ህፃናት ውስጥ ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር የቅርብ ግንኙነት ይኖሮታል፤ በጋራ ለልጅዎ የተሻለ የሚሉትን ነገር ይወስናሉ፡፡

4. **በመዋለ ህፃናት ውስጥ ለልጄ የሚሆን ቦታ እንዴት ማግኘት እችላለው?**

የእርሶን ጉዳይ በሚመለከት የሚያናግሩት ሰው **[... ስም እና የግለሰቡን መረጃ እዚህ ጋር ያስገቡ...]** በማዘጋጃ ቤት ውስጥ ለቦታ በማመልከት እና ምን ያህል ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል በማስላት ይረዶታል፡፡

5. **ምን ያህል ያስከፍላል?**

- ልጅዎ ምናልባት በሳምንት የ20 ሰዓታት በነፃ በመዋለ ህፃናት ወስጥ ለመቆየት የሚያስችል እድል ሊኖር ይችል ይሆናል፡፡
- ገቢዎ ዝቅተኛ ከሆ፤ የወላጆች ክፍያ የሚቀንስበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡
- በመዋለ ህፃናቱ ውስጥ ከአንድ በላይ ልጅ ካሎትም ክፍያ የሚቀንስበት ሁኔታ አለ፡፡

***ለልጅዎ መልካም የሆነ ጅማሬን ይስጡ!***